# የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ክፍል ሰባት

1. ከሚከተሉት የልብ ወለድ አላባውያን መካከል የልብወለዱ አከርካሪ ወይም የጀርባ አጥንት በመባል የሚታወቀው አላባ (የልቦለድ ሙያዊ ቃል) የቱ ነው ?

   ሀ) አንፃር　　ለ) ትረካ　　ሐ) ግጭት　　መ) ጭብጥ

2. ከአጭር ልብወለድ አላባውያን መካከል የልብወለዱ ታሪክ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክተው አላባ የቱ ነው ?

   ሀ)ግጭት　　ለ) ሴራ　　ሐ) መቼት　　መ) ጭብጥ

3. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ስለ አጭር ልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) የአጭር ልቦለድ ሀፀ ባህርያት በታሪኩ ውስጥ በርካታ ግጭቶች የገጥሟቸዋል

   ለ) የአጭር ልቦለድ ደራሲ የራሱን ፍልስፍና ዘርዘር አድርጎ እንዲያቀርብ ያስችላል

   ሐ) አጭር ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አንድ ቅንጫቢ ሊሆን ይችላል

   መ) የአጭር ልቦለድ ጭብጥ ነጠላ ወይም አንድ ነው

4. ................ በልብወለድ ፅሁፍ ደራሲው ከልቡ አመንጭቶ የሚፈጥራቸው የገሃዱ ዓለም ሰዎች ወኪሎች ናቸው ::

   ሀ) አንፃር　　ለ) ገፀ ባህርያት　　ሐ) ተደራሲያን　　መ) ደራሲያን

5. .................. አንዱ ገፀ ባህርይ ከሌላው ገፀ ባህርይ ጋር የሚፈጥረው እሰጥ አገባ ነው ::

   ሀ) አንፃር　　ለ) ግጭት　　ሐ) ትልም ( ሴራ)　　መ) ጭውውት

6. እውነትና ንጋት..................

   ሀ) እያደር ይጠራል　　ለ) ደማቅ ናቸው

   ሐ) አያስታውቅም　　መ) መልስ የለም

7. ሌባን ሌባ ቢሰርቀው......................

   ሀ) አባረረው　　ለ) እንዴት ይደንቀው

   ሐ) መሬት ላይ ጣለው　　መ) ወዴት ይሄደው

LIVEWORKSHEETS

8. **<u>ደመ መሪራ</u>** የዚህ ፈሊጥ ፍቺ

ሀ) ሃይለኛ ለ) ጎበዝ

ሐ) ነገር የሚከብድበት መ) እልከኛ

9. **<u>እጅ አጠረው</u>** ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) ከበደው ለ) ቸገረው

ሐ) ልብሱ አጠረው መ) ደከመው

10. **<u>ሀረግ መምዘዝ</u>** ለሚለው ፈሊጥ ፍቺ የሚሆነው

ሀ) አትክልት መትከል ለ) ዘር መቁጠር

ሐ) አረጅም መሆን መ) መታገስ

11. ዕከሊት **<u>ጭራ ቀረሽ</u>** ናት ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) ከልፍልፍ ናት ለ) ቀዥቃዣ ናት

ሐ) ቀጭን ናት መ) ሃ እና ለ

12. ጊዜ የሰጠው ቅል.................

ሀ) ከድንጋይ ይከብዳል ለ) ድንጋይ ይሰብራል

ሐ) አኩል ይበቅላል መ) ይጠነክራል

13. እማን ላይ ቆመሽ................

ሀ) የት ትመጫለሽ ለ) ማንን ታሚያለሽ

ሐ) ወዴት ትሄጃለሽ መ) ሙች ትመጫለሽ

14. ለሆዳም በሬ...................

ሀ) ጭድ ያዝለታል ለ) ዱላ ያዝለታል

ሐ) ውሃ የጠጣል መ) ለ እና ሐ

15. ‹‹የሰው ደግ›› እና ‹‹ደግ ሰው›› የተሰኙት ሀረጎች በቅደም ተከተል ሲቀመጡ ትክክለኛው የትኛው ነው?

ሀ. ግሳዊ ሀረግና ቅፅላዊ ሀረግ ሐ.ቅፅላዊ ሀረግና ስማዊ ሀረግ

ለ. ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ መ.ግሳዊ ሀረግና መስተዋድዳዊ ሀረግ

LIVEWORKSHEETS

መንገደኛው ሁሉ እሳት ሜሪ ነው፣

የኝን ገል አደራ ሰው እንዳይነካው።

16. የዚህ ቅኔ ሀብረ ቃል የሚሆነው

ሀ) ገል ለ) ያንንገል አደራ ሐ) አደራ መ) እንዳይነካው

17. የዚህ ቅኔ ወርቁ

ሀ) ያንን ገላ ሌላ ሰው እንዳይነካው ለ) ያንን ሸክላ ሰው እንዳይነካው

ሐ) እሳት መሜሪያውን ገል ሰው እንዳይነካው መ) ለ እና ሐ

18. የዚህ ቅኔ ሰም የሚሆነው

ሀ) ያንን ገላ ሌላ ሰው እንዳይነካው ለ) ያንን ሸክላ ሰው እንዳይነካው

ሐ) እሳት መሜሪያውን ገል ሰው እንዳይነካው መ) ለ እና ሐ

19. አይጥ በበላ....................

ሀ) ድመት እሮጠች ለ) ዳዋ ተመታ

ሐ) ድመት ተያዘች መ) ለ እና ሐ

20. አንድን ሰበብ ወይም መነሻ ምክንያት መሰረት አድርጎ መደምደሚያ ላይ የሚደረስበት ሂደት ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ) ውጤት ለ) ምክን ያት ሐ) መንስዔ መ) ሁሉም

21. በድርጊት ተቀባዩ ወይም ተሳቢ አካል ላይ ትኩረት የሚያደርገው አረፍተ ነገር አይነት የቱ ነው ?

ሀ) ገቢር አረፍተ ነገር ለ) ተገብሮ አረፍተ ነገር

ሐ) ጥያቄያዊ አረፍተ ነገር መ) ነጠላ አረፍተ ነገር

22. ማን ያርዳ...............፣ ማን ይናገር ............. የሚለውን ያልተሟላ ምሳሌያዊ አነጋገር ሊያሟላ የሚችለው :

ሀ) የነበረ ፣ የቀበረ ለ) የቀበረ ፣ የነበረ

ሐ) የወረረ ፣ የፈጠረ መ) የወገረ ፣ የበረረ

LIVEWORKSHEETS

23. ከሚከተሉት ማሳሌያዊ አነጋገሮች አንዱ በፍቺ ትርጉም ልዩ ነው ፡

ሀ) ሲሮጡ የተጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ለ) የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

ሐ) አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ መ) የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ

24. ...................... የአንደን ነገር አሰራር፣ አፈፃፀም፣ ምንነት፣ ባህርያት፣ ቅርጽ፣ አይነት፣ መጠን፣ አገኛ ኘት፣ ጠቀሜታ ወይም ጉዳት ወዘተ ለማብራራት የሚፃፍ የድርሰት ዓይነት ነው።

ሀ) ስዕላዊ ለ) አመዛዛኝ ሐ) ገላጭ መ) ተራኪ

25. የመስሪያቤት ደብዳቤ ስንጽፍ መለያ ቁጥሮችን እና ዓመተ ምህረትን ለመለየት የምንጠቀምበት ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ) ቅንፍ ለ) ነጠላ ሰረዝ ሐ) እዝባር መ) ሁለት ነጥብ

26. ወደሽ ከተደፋሽ....................

ሀ) ቶሎ በተነሳሽ ለ) ቶሎ ተመለሽ

ሐ) ቢረግጡሽ አይከፋሽ መ) ለ እና ሐ

27. ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃላት ተከታትለው ሲመጡ ለመለየት የምንጠቀመው ሥራዓተ ነጥብ የትኛው ነው ?

ሀ) ድርብ ሰረዝ ለ) ነጠላ ሰረዝ

ሐ) ጥያቄ ምልክት መ) ቅንፍ

28. ሊቁ እንዲህ ብሏል፤ **የማውቀው አለማወቄን ነው**። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የሚገባው ሃሳብ የትኛው ነው?

ሀ) እንዲህ ብሏል ሐ) አለማወቄን ነው

ለ) ሊቁ እንዲህ ብሏል መ) የማውቀው አለማቀቄን ነው

29. ከሚከተሉት አንዱ ተገቢ ስር ዓተ ነጥብ በተገቢ ቦታ ላይ ተጠቅሟል

ሀ) ብስኩት ፣ በዱቄት፣ በእርሾ፣ በዘይትና በስኳር ይሰራል

ለ) ብስኩት በዱቄት፣ በእርሾ፣ በዘይትና በስኳር ይሰራል

ሐ) ብስኩት ፣ ዱቄት፣ በእርሾ፣ በዘይትና በስኳር ይሰራል

ሀ) ብስኩት ፣ በዱቄት፣ በእርሾ፣ በዘይትና በስኳር፣ ይሰራል

30. **<u>ቀንበር ሰበረ</u>** ለሚለው ፈሊጥ ፍች የሚስማማው የቱ ነው?

ሀ) ጎረመሰ ለ) ጠነከረ ሐ) ህግ ተላለፈ መ) መመሪያ አከበረ

LIVEWORKSHEETS

31. የምጣዱ እያለ.......................................

ሀ) የእንቅቡ ተንጣጣ

ለ) የሌላው አረረ

ሐ) የእንቅቡ አይን አወጣ

መ) ሌላው እንቅልፍ አጣ

32. ላም ባልዋለበት....................................

ሀ) እረኘነት

ለ) ኩበት ለቀማ

ሐ) ጥጃ ፍለጋ

መ) ልፋት

33. ከበሮ በሰው እጅ ያምር ......................................

ሀ) ሲሙቱት ያደናግር

ለ) ሲይዙት ደስ ይል

ሐ) ሲይዙት ያደናግር

መ) ሲይዙት ያምር

34. አፍንጫ ሲመታ ...........................................

ሀ) አይን ያለቅሳል

ለ) አይን ይደማል

ሐ) አይን ያያል

መ) ጆሮ ይጩሃል

35. ከሞኝ ደጃፍ ...........................................

ሀ) በግ ይወሰዳል

ለ) ልጅ ይቻወታል

ሐ) ሞፈር ይቆረጣል

መ) ሰው ይሰበሰባል

LIVEWORKSHEETS